# ለሠላም፣ ለልማትና ለዴሞክራሲ ልዕልና ሲሉ ለወደቁ ሰማዕታት የሚቆም ሐውልት!

ሙሉቀን ተሻለ 03/04/14

ከመሰንበቻው ፋክት መጽሔት በቅጽ 2 ቁጥር 34 በየካቲት 2006 ዓ.ም ዕትም ላይ ቴዎድሮስ ተ/አረጋይ በተባሉ ጸሐፊው አማካኝነት "የመከላከያ ሠራዊቱ ዕድሜ ስንት ነው?" በሚል ርዕስ ፅሑፍ አቅርቦ ነበር። ለፅሑፉ መነሻ የሆነው በቅርቡ የኢ.ፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት በምድር ኃይል ቅጥር ግቢ ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ የሠራዊት ቀንን ባከበረበት ወቅት፣ በስፍራው ለሠላም፣ ለልማትና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሲሉ ክቡር ህይወታቸውን ለከፈሉ ሰማዕታት የመታሰቢያ ሐውልት ለማቆም የመሰረት ድንጋይ መጣሉን ተከትሎ በተፈጠረ የተሳሳተ ስሜታዊ ግልቢያ ነው። እናም በዚህ ፅሑፌ ፀሐፊው (አላዋቂ ተቺው ብላቸው ሳይሻል አይቀርም) በግልብ ሐተታቸው ካሰፈሩት እንዲሁም የሰማዕታት ሐውልቱ እንዲገነባ ከታሰበበት ዕውነታ ፍፁም ባፈነገጠ መረጃቸው ላይ ተመረኩዤ ምላሽ ለመስጠት እሞክራለሁ፡፡

እንደሚታወቀው 'የመከላከያ ሠራዊት ዕድሜ ስንት ነው?' ተብሎ ሲጠየቅ፣ በቅድሚያ ወደ አእምሮአችን የሚመጣው 'የየትኛው ዘመን አሊያም በየትኛውም መንግስት የተገነባው የመከላከያ ሠራዊት ነው?' የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ ይሁንና 'የመከላከያ ሠራዊቱ ዕድሜ ስንት ነው?' ከተባለ፣ ኢትዮጵያ የተባለች ሀገር ከተፈጠረችበት አንስቶ ልዕልናዋን ከወራሪዎችና ከተስፋፊዎች እንዲሁም ህዝብን ከጥቃት የሚከላከል ሠራዊት ወይም መደበኛ ሰራዊት ከተቋቋመበት አንስቶ ያለው ጊዜ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ ዳሩ ግን እዚህ ላይ በአንድ መንግስት የተገነባ የመከላከያ ኃይል፣ በሌላ መንግስት ከተገነባው ሊለያይባቸው የሚያስችሉ የየራሳቸው ባህሪ እንዳላቸው መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ እናም ከዚህ ዕውነታ ተነሰተን የሀገራችን የመከላከያ ሠራዊት ዕድሜን በጥቅሉ ለመናገር የሚችግር አይደለም፡፡ ምክንያቱም ሀገራችን በማንም ሳትደፈር ተከብራ እንድትኖር

ከጥንት ዘመን ጀምሮ የመከላከያ ሠራዊቱ የሀገሩን ዳር ድንበር እያስከበረ፣ ለቀጣይ ትውልድ ጀግንነቱን እያወረሰ የመጣ እንዲሁም ዳግም ለማያገኛት ህይወቱ ሳይሳሳ የህዝቦችን የዘመናት የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ጥያቄዎችን ለመመለስ የተሰዋ መሆኑ ከማንም የተሰወረ ሃቅ ስለሆነ ነው፡፡ እናም የሠራዊቱ ዕድሜ ከሀገሪቱ ዕድሜ ጋር ያልተናነሰ መሆኑን ለመገመት የሚያዳግት አይመስለኝም፡፡ አዎ! ዛሬ ላይ እንደ የአድዋ ድል ዓይነት የጥቁር ህዝቦች አይበገሬነትን የሚያወጁ በዓላትን የምንዘክረው ብሎም ውድ የህዝብ ልጆች የተሰውለትን ታላቅ የትግል ውሎ እያስታወስን የምናከብረው የዚህ ሃቅ ማስረገጫዎች ናቸው።

ይሁን እንጂ የፋክት መጽሔቱ አቶ ቴዎድሮስ የተሳሰተ ጭፍን አመለካከትና እምነት በመያዝ የሀገራችንን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የዘመናት ሰቆቃና ብሶት አልመለከትም ብለው ዱር ቤቴ ላሉትና የእነርሱን ፈለግ ተከትለው በሠራዊትነት ለሀገራቸው ውድ ህይወታቸውን ለከፈሉ የህዝብ ልጆች መታሰቢያ ይሆን ዘንድ በምድር ኃይል ቅጥር ግቢ የሚቆመውን ሐውልት የተቹበት አካሄድ ውሃ የሚቋጥር አይደለም። ሰውዬው የመረጃ እጥረት ብቻ ሳይሆን፣ ጭልጥ ያለ የተዛባ አመለካከት በውስጣቸው መያዛቸውም ለፃፉት አራምባና ቆቦ ትርክት ምክንያት ሆኗቸዋል ባይ ነኝ።

ሰውዬው ለሰላም፣ ለልማትና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ክቡር መስዋዕትነት ለከፈሉት የኢፌዴሪ መከላከያ ሰራዊት አባላት የመታሰቢያ ሐውልት ለመገንባት የመሠረት ድንጋይ መጣሉ ምን እንዳናደዳቸው ግልፅ ባይሆንም፤ ስነ-ስርዓቱን በቴሌቭዥን መስኮት መከታተላቸውን በመጥቀስ ያለፈው የአምባገነኑና የሰው በላው የደርግ ሠራዊት በውስጡ የለም ሲሉ ይደመድማሉ፡፡ የድምዳሜያቸው ምክንያት ግን ግልፅ የሆነ ጥላቻ መሆኑ የሰነዘሯቸው በርካታ አግድሞሻዊ አባባሎች ለመረዳት አያዳግትም።

እርግጥ አቶ ቴዎድሮስ የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት ቀን ለሁለተኛ ጊዜ የካቲት 7/2006 ዓ.ም በምድር ኃይል ግቢ "ለህገ - መንግስቱና ለህዳሴ ስኬት ጉዞ የሠላምና የልማት ኃይል ሆነን እንቀጥላለን" በሚል መሪ ቃል በተከበረበት ወቅት፤ መረጃን ለመከታተል፣ ተከታትለውም የፈለጉትን አስተያየት በመስጠት መጻፋቸው እንዲሁም ለዚህ መብት

ያበቋቸውን ሰማዕታት ብሎም ዛሬ ላይ በአስተማማኝ ሰላማዊ ምህዳር ውስጥ ሆነው ያሻቸውን እንዲፅፉ ህይወታቸውን እየከፈሉ ያሉትን ብርቅዬ ወገኖችን ዘንግተዋቸዋል። እናም ይህን እውነታውን እንደማንኛውም ዜጋ ስመለከተው፣ ግለሰቡ ሃቁን በማንሻፈፍ የተሳሳተ መረጃ ለህዝቡ ለማቅረብ መሞከራቸው አንባቢን ከመናቅ ባሻገር፣ ትዕዝብት ላይ የሚጥላቸው ይመስለኛል፡፡ እስቲ ለማንኛውም ሰውዬው ስላነሱት የደርግ ስርዓት ሠራዊት ጉዳይ እናምራ።…

እንደ ፀሐፊው መረጃ አልቦ ትችት የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት ለሁለተኛ ጊዜ ቀኑን ሲያከብርና ለሀገር ዳር ድንበርና ለህዝብ አለኝታ ሲሉ ውድ ህይወታቸውን መስዋዕት ላደረጉ የህዝብ ልጆች የሐውልት እንዲቆምላቸው የመሰረተ ድንጋይ ሲቀመጥ፤ በደርግ አምባገነናዊ ስርዓት ወቅት ሀገራቸውን በውትድርና ሲያገለግሉ የነበሩትን የቀድሞ የሠራዊት አባላትን አልተመለከትኩም ብለዋል፡፡ ይህም በእርሳቸው እምነት የቀድሞ የመከላከያ ሠራዊት አባላት ከአሁኑ የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት ውስጥ አልተቀላቀሉም የማለት ያህል ይመስለኛል፡፡ ግና በእኔ እምነት ሰውዬው ስለሚያወሩት ነገር እንጥፍጣፊ ዕውቀት ያላቸው አይመስለኝም፡፡ ለምን? ቢሉ፤ የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት በደንብ ቁጥር 27/1988 ዓ.ም ብሔራዊ ተዋጽኦን ባካተተ መልኩ ሲደራጅና በወቅቱም መንግስት በደርግ ስርዓት ውስጥ በውትድርና ሀገራቸውን ሲያገለግሉ የነበሩትን ፍቃደኛ የሆኑ አባላት ሰራዊቱን እንዲቀላቀሉ ባቀረበው ጥሪ መሰረት እስካሁን ድረስ ለሀገራቸው እየሰሩ በመሆናቸው ነው።

እናም አቶ ቴዎድሮስ ምናልባትም ‘ፀሐፊ ነኝ’ አሊያም ‘እንደ ጋዜጠኛ ነው’ የምሰራው የሚሉ ከሆነ ይህን ነባራዊ ዕውነት ከሚመለከተው አካል ማጣራትና በትክክለኛው መልኩ መረዳት በተገባቸው ነበር። ግና ዓላማቸው እንደ ማንኛውም ፅንፈኛ ያገኙትን ብጣቂ ወሬ ይዘው አሉባልታን ማራገብ ስለሆነ ‘ለምን ይህን አደረጉ?’ ተብለው ሊወቀሱ አይችሉም። ኧረ እንዲያውም ሃቁን አጣርተው ቢፅፉ በእነ አቶ ተመስገን ደሳለኝ “የተልኮ” ኤዲቶሪያል ፖሊሲ በሚመራው ፋክት መፅሔት ላይ ፅሁፋቸው ‘ወግድ!’ መባሉ አይቀርም።

ታዲያ እዚህ ላይ በወቅቱ ወደ አዲሱ መከላከያ ሰራዊት ሁሉም የቀድሞው ሰራዊት አባላት ተቀላቅለዋል እያልኩ አለመሆኑ ግንዛቤ ሊያዝልኝ ይገባል። እንደሚታወቀው አምባገነኑ

የደርግ ስርዓት በወቅቱ 'በጠላቶቼ የተከበብኩ ነኝ' በሚል የውጭ ፖሊሲ የሚመራና እስከ ግማሽ ሚሊዮን የሚደርስ እጅግ ግዙፍ ኃይል ገንብቶ ነበር። እናም ይህን ከጥቁር አፍሪካ በብዛቱ ከቀዳሚዎቹ ተርታ የሚመደብ ኃይልን ባዶ ካዝናን ለተረከበው የኢህአዴግ ኃይል ሙሉ ለሙሉ ለመቀበል ፈፅሞ የሚቻለው አይደለም። ምክንያቱም የሀገራችን ኢኮኖሚ ሊሸከመው ስለማይችል ነው። በመሆኑም ቁጥራቸው በርከት ያለና ለሀገራቸው ለመስራት ፈቃደኛ የሆኑ የቀድሞ ሰራዊት አባላትን በውስጡ ለማካተት ተገድኋል። እናም እነዚህ አባላት በየተሃድሶው ማዕከላት በህዝባዊ ባህሪ እንዲገነቡ ከተደረገ በኋላ፣ ከነ ማዕረጋቸውና ከነ ጥቅማጥቅሞቻቸው የአዲሱ ሰራዊት አባል በመሆን ዛሬም ድረስ ህገ -መንግስታዊ ተልዕኳቸውን በፅናት እየተወጡ መሆናቸውን በቅንነት መረዳት የሚገባ ይመስለኛል። እንዲያውም አቶ ቴዎድሮስ በዚህ ፅሑፋቸው ሆን ብለው 'መረጃ እርሙ' ለመሆን ፈለጉ እንጂ፤ እነዚህ አባላት ቀደም ሲል በውትድርናው ዓለም ውስጥ ያካበቱትን ልምድ ለአዲሱ ሠራዊት በማካፈል መከላከያ እያከናወነ በሚገኘው የዘመናዊ ሠራዊት ግንባታ ሂደት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አበርክተዋል፤ እያበረከቱም ነው፡፡

ያም ሆኖ ግን አቶ ቴዎድሮስ 'በደርግ ሥርዓት የነበረው ሠራዊት የነበረው ህዝባዊ ባህሪ የትም እንዳልባሌ መጣሉ የታየ እውነት ነው' ያሉት አስገራሚ አባባልን መመልከት ሰውዬው አሁን ያለውን የኢፌዴሪ መከላከያ ሰራዊትን ምን ያህል ጥላሸት ለመቀባት እየታተሩ መሆናቸውን ለመገንዘብ አያዳግትም። ግና ለዚህ ያፈጠጠና ያገጠጠ ውሸት የማወቀውን ያህል ምላሽ ከመስጠቴ በፊት፤ ለመነሻ ግንዛቤ ይረዳን ዘንድ በቅድሚያ ስለ ኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት መደበኛ ጦር አመሰራረት፣ አደረጃጀትና በየዘመናቱ ስለተገነባበት ባህሪያት ምንነት በጥቂቱ ለውድ አንባቢዎቼ ማውጋት አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። እናም በወፍ በረር ቅኝት 'እነሆ' ልበል።...

በኢትዮጵያ ታሪክ መደበኛ ሠራዊት የተቋቋመበት ጊዜው በትክክል ባይታወቅም ቅሉ፤ መደበኛ የሆነ የሠራዊት አደረጃጀት የተጀመረው በአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግስት እንደሆነ ይነገራል፡፡ ይህ ዘመን ከ1847 እስከ 1864 ዓ.ም ነው፡፡ አፄ ቴዎድሮስ ከምዕራባውያን የተለያዩ ተሞክሮዎችን በመውሰድ፣ በሠራዊት ውስጥ ሶስት መሰረታዊ ለውጦችን ማድረግ መቻላቸው የታሪክ ድርሳናት ያመለክታሉ፡፡ እነዚህም አንዱ ሠራዊቱን

በቴክኒካዊ ዕውቀት ለማገዝ በጋፋት የቴክኒክ ትምህርት ቤት በመክፍት ስልጠናዎች መጀመራቸው ሲሆን፣ ሁለተኛው ሠራዊቱን ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ለማስታጠቅ በነበራቸው ፍላጎት በውጭ ሃይሎች በመታገዝ 'ሴባስቶፖል' በመባል የሚታወቀውን መድፍ ማምረት ከመቻላቸው በላይ፣ የሠራዊቱን የመሣሪያ ግምጃ ቤት መቅደላ ላይ ለመመስረት መሞከራቸው ነው፡፡ ሶስተኛው ደግሞ የወቅቱ የሠራዊት መደበኛነት ይኖረው ዘንድ የሠራዊቱን አደረጃጀት መልክ እንዲይዝ ለማድረግ ያደረጉት ጥረት ነው። ይህ ጅማሬም ሠራዊቱ ደመወዝ እንዲከፈለው፣ በተዋረድ የዕዝ ሰንሰለት እንዲኖረውና በየደረጃው የሚመጥን ማዕረግ እንዲሰጠው በማድረግ፣ በወታደራዊ አመራር ግንኙነት መቀላጠፍ አመቺ ሁኔታ ፈጥረዋል፡፡ በዚያ ዘመን ለሠራዊቱ ደመወዝ መክፈል መጀመሩ ወታደሩ ለሙያው ክብር እንዲሰጥ ከማድረግ ባለፈ፣ የንጉሱ ወታደር ቀደም ሲል የአርሶ አደሩን እህል እየዘረፈ የሚበላበት ልምድ በሂደት እንዲቀረፍ አድርጓል፡፡

አፄ ዮሐንስ ከ1864 እስከ 1881 ዓ.ም ኢትዮጵያ ያስተዳደሩ ሲሆን፣ በአጼ ቴዎድሮስ ጊዜ የነበረውን የሠራዊት አደረጃጀት እንዲቀጥል በማድረግ አሻራ ጥለው አልፈዋል፡፡ በ1881 ዓ.ም አፄ ዮሐንስ ከደርቡሾች ጋር ባደረጉት ውጊያ የህይወታቸውን ማለፍ ተከትሎ በምትካቸው አጼ ምንሊክ ተተኩ፡፡ የኢትዮጵያ ጦር ለመጀመሪያ ጊዜ ዩኒፎርም የለበሰውም በዚሁ ዘመነ መንግስት እንደሆነ ይነገራል፡፡ ሌላው ተጨማሪ ለውጥ ደግሞ በ1908 ዓ.ም የካቢኔ ሚኒስቴር ለመጀመሪያ ጊዜ ሲቋቋም፣ ከተመሰረቱት የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች አንዱ የጦር ሚኒስቴር መሆኑ ነው፡፡ ይህ እርምጃም ሰራዊቱ ወደ መደበኛ የጦር አደረጃጀት እንዲሸጋገር ፈር የቀየሰ ተግባር ነው ማለት ይቻላል፡፡

አጼ ምንሊክ የጣሊያን ፋሽሽት ሀገራችንን በግዙፍ ወታደራዊ ሃይልና ዘመናዊ የጦር መሣሪያ በታጠቀ ሰራዊት ወረራ በፈጸመብን ወቅት፣ መላው የኢትዮጵያን ህዝብ በማስተባበር መርተው ወራሪውን ሃይል በአሳፋሪ ሁኔታ ድል ነስተው፣ ለሀገራችን ብቻ ሳይሆን ለመላው ጥቁር አፍሪካውያን ወንድምና እህቶቻችን ኩራት ሆነዋል፡፡ ሀገራችንም አፄ ሚኒልክ የወቅቱ ጀግኖች አርበኞቻችን ላበረከቱት ታላቅ አስተዋጽኦ በተለያዩ ቦታዎች ሐውልቶች አቁማላቸዋለች፡፡ በኢትዮጵያ የውትድርና ታሪክ የመጀመሪያው መደበኛ ጦር

የክብር ዘበኛ በሚል የሚታወቀውን ሠራዊት ነው፡፡ የዚሁ ጦር ጥንስስ የተጣለው ራስ ተፈሪ ገና አልጋ ወራሽ እንደሆኑ ሲሆን፤ ተግባሩም ራስ ተፈሪን መጠበቅ ነበር፡፡

ጊዜ ጊዜን እየወለደ ሲመጣ አፄ ኃይለስላሴ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ያደርሱት የነበረው ጭቆና በመባባሱ ሳቢያ በ1966 ዓ.ም ደርግ በመፈንቅለ መንግስት ወደ ስልጣን ለመምጣት ምክንያት ሆነው፡፡ አ ኃይለስላሴ በመንበረ ስልጣን ጊዜያቸው ወቅት ንጉሱንና ስርዓቱን ሊያስታውሱ የሚችሉ በክልል ከተሞችና በመዲናችን አዲስ አበባ በርካታ ሐውልቶችን አቁመው አልፈዋል፡፡…በንጉሱ እግር የተተካው የደርግ አምባገነናዊ ጁንታም በቁጥርና በታጠቀው መሣሪያ ብዛት ብሎም ዓይነት ግዙፍ ነበር፡፡ ነገር ግን በሥነ - ምግባርና በብቃቱ በእጅጉ የወረደ ነበር፡፡ በተለይም ፀረ- ህዝባዊነቱ ወደር የለውም። ስርዓቱ ስልጣኑን ለማቆየት ሲል በቀይ ሽብር አማካኝነት ከግማሽን ሚሊዮን በላይ ዜጎችን መጨፍጨፉ የሚዘነጋ አይደለም። ህዝብን እንደ ጠላት በመቁጠርና ጥያቄዎቹን በሃይል ለመደፍጠጥ ሲል በሀገራችን የተለያዩ ስፍራዎች የፈፀማቸው የለየላቸው ጭፍጨፋዎች ቁስል ዛሬም ድረስ ከህዝቡ ህሊና ውስጥ አልሻረም። ታዲያ እዚህ ላይ የደርግ ሰራዊት በህዝባዊ ጨፍጫፊነቱ የሚታወቅ ከመሆኑም በላይ፤ ደርግ በስልጣን ላይ በቆየባቸው አስራ ሰባት ዓመታት ስርዓቱን ሊያስታውሱ የሚችሉ በርካታ ሐውልቶች መገንባቱን ልብ ይሏል፡፡ ከእነዚህ ሐውልቶች ውስጥ በመዲናችን አዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል አካባቢ የሚገኘውና “ድላችን” የተሰኘው ሐውልት ተጠቃሽ ነው፡፡…

…እንግዲህ ከዚህ ጠቅለል ያለ ሃቅ የምንገነዘበው ነገር ቢኖር ባለፉት ስርዓቶች ይደራጁ የነበሩት የመከላከያ ሰራዊቶች ከውትድርና ሙያ አኳያ ጥለውት ያለፉት አሻራ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ተግባራቸው ግን በወቅቱ የነበሩትን ነገስታትንና አምባገነኖችን ፍላጎት ማስፈፀም እንጂ፣ አንዳቸውም ህዝቡን የሚወክሉ አልነበሩም። እንዲያውም ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት ፀረ-ህዝብነትን እንደ ዋነኛ መርሃቸው የያዙ ናቸው ብል ከዕውነታው ብዙም የምርቅ አይመስለኝም። ታዲያ እነዚህ ሃቆች የፋክት መፅሔቱ አቶ ቴዎድሮስ ‘የደርግ ሰራዊት ህዝባዊነት እንደ አልባሌ የትም ተጥሏል’ ወዳሉትና እኔም ኋላ ላይ እመለስበታለሁ ወዳልኩት ጉዳይ ይወስደናል።

ውድ አንባቢዎቼ! ኸረ ለመሆኑ የደርግ ሰራዊት በምን ዓይነት የተቃውሞ ስሌት ይሆን ሰውዬው ያለ አንዳች ሃፍረት 'ህዝባዊ ነው' ሊሉን የከጀሉት?...ለእርሳቸው ሰራዊቱና ስርዓቱ ከአምስት መቶ ሺህ በላይ የፈጁት የኢትዮጵያ ህዝብ ጥፋተኛ ይሆን እንዴ?...ምናልባትም አቶ ቴዎድሮስ አሁን ያለውንና የህዝቦችን የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ጥያቄዎች የመለሰውን የኢፌዴሪ መከላከያ ሰራዊትን የማይታበል ዝና እና ህዝባዊነትን በጭፍን ጥላቻ ጥላሸት ለመቀባት ሲሉ፤ የዜጎችን ደም እንደ ጎርፍ በማፍሰስ በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ቤተሰብ ውስጥ የሐዘንና የሰቆቃ መሪር ትንግርትን ጥሎ ያለፈና ህዝብን በጥይት ከገደለ በኋላ መልሶ የጥይቱን ዋጋ የሚያስከፍል ሰራዊትን "ህዝባዊ" ማለታቸው ሰውዬው ለህዝብ ያላቸው ንቀት ምን ያህል እንደሆነ የሚያሳይ ነው። ግለሰቡ ስለ ህዝብ ያላቸው እጅግ የተንሸዋረረ ዕይታን የሚያሳብቅ መሆኑም እንዲሁ። አፍቃሬ ደርግነታቸውንም ጭምር።

ያም ሆነ ይህ ሰውዬውን ቢያሳዝናቸውና ዛሬ ላይ ሆነው የወረቀት አንበሳ ሆነው 'አንበሳዬ' እያሉ ቢያላዝኑም፤ ህዝባዊነትንና ፅናትን በተላበሱት፣ በመላው የኢትዮጵያ ህዝቦች በሚደገፉትና ለዛሬው የኢፌዴሪ መከላከያ ሰራዊት እርሾ በመሆን በደማቸው ታላቅ ታሪክ በፃፉት ውድ የህዝብ ልጆች ሰው በላው ስርዓት ግብዓተ-መሬቱ ተፈፅሟል። ከደርግ ውድቀት በኋላም የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በፍላጎታቸው አዲሱን ፖለቲካዊና ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰብ ለመመስረት የሚያስችላቸው ሰላማዊ ሁኔታ መፍጠራቸውም እንዲሁ።:፡ ወደውና ፈቅደውም በአንድነት የጋራ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መሰረት የሚሆን ህገ - መንግስት በጋራ መክረው አፅድቀዋል፡፡ በዚህም የጋራ የሆነችውን ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያን መስርተዋል፡፡ የሀገሪቱን ሉዓላዊነት የሚያስከብር፣ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦችን ሚዛናዊ ተዋጽኦ ያካተተና ከፖለቲካ ድርጅት ወገናዊነት የነጻ እንዲሁም ህዝባዊ ወገንተኝነቱ የጠነከረ መከላከያ ሠራዊትን የካቲት 7 ቀን 1988 ዓ.ም በአዋጅ አቋቁመዋል፡፡

ታዲያ እዚህ ላይ አቶ ቴዎድሮስ ራሳቸው ተወዛገበው ሌሎችን ለማደናገር ስለሞከሩበት "ህዝባዊነት" ለማወቅ ከፈለጉ የተግባሩ ተምሳሌት ወደ ሆነው የኢፌዴሪ መከላከያ ሰራዊት ጎራ ማለት እንዳለባቸው፣ አሊያም ከሌሎች ጠይቀው ማወቅ እንደሚኖርባቸው

ሳልጠቁማቸው አላልፍም። ምክንያቱም ሰራዊቱ ከራሱ በፊት ለህዝብና ለሀገር እንደሚሰዋ፣ ምንግዜም የተሟላ ስብዕና እንዳለው፣ ያልተሸራረፈ ዴሞክራሰያዊ አስተሳሰብ ባለቤት እንደሆነ እንዲሁም በማንኛውም ወቅት ወይም ሁኔታ በአነስተኛ ኪሳራ ድልን የሚያፍስ የህዝብ አለኝታ መሆኑን በቀላሉ ስለሚረዱ ነው። ህዝባዊ ወገንተኝነቱን ስንቁ ያደረገው ይህ ሰራዊት በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ለማንም የማይወግንና ማንኛውንም የሰው ዘር በእኩል ዓይን የሚመለከት መሆኑን ከአፍሪካ ህብረት እስከ የተባበሩት መንግስታት ድረስ ተሰጠው የሰላም ማስከበር አመኔታን የተሰጠውን ይሁንታ ብቻ በአስረጅነት ሊወስዱት ይችላሉ። እናም ህዝባዊ ሰራዊት ማለት በየሄደበት ሲቪሎችን የሚያከብርና ለሰዎች ሲል የሚሰዋ የህዝብ አጋር እንጂ፤ በአምባገነናዊነት ደዌ ተለክፎ የተገላቢጦሹን ሲከውን የኖረው የሰውዬው 'ሰራዊት' አለመሆኑን ለአቶ ቴዎድሮስ መንገር ከፅድቅ እንጂ ከኩነኔ የሚቆጠርብኝ አይመስለኝም። ምንም እንኳን የፀረ-ህዝቦች አብነት ያው ፀረ-ህዝብ መሆኑን ባውቅም። እናም ግለሰቡ ወደ ዕውነታው ጎዳ መለስ ብለው ማየትን እንደ ነውር ቢቆጥሩትም፣ የኋላ ኋላ በህዝቡ ዘንድ ከትዝብት ጋር "ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ..." ከመባል የሚያመልጡ አይመስለኝም። ምክንያቱም ህዝቡ በእኩይ ምግባሩ እንደ እጁ ጣቶች ጠንቅቆ የሚያውቀውንና ሰው በላውን የደርግ ሰራዊት "ህዝባዊ ነው" በሚል የውሸት ክምር በአደባባይ ሲያሞካሹት ተመልክቷልና!

ውድ አንባቢዎቼ! 'የመከላከያ ሠራዊቱ ዕድሜ ስንት ነው?' ሲሉ በፋክት መጽሔት ላይ ቁዘማቸውን ያስነበቡን አቶ ቴዎድሮስ በየትኛው ስርዓት ስለተገነባው የመከላከያ ሠራዊት እንደሆነ በግልጽ ያሉት ነገር የለም፡፡ ቀድም ብዬ ታሪክን በማጣቀስ ለማስገንዘብ እንደሞከርኩት በሀገራችን በየስርዓቱ የተገነቡ የመከላከያ ሠራዊቶች ለህዝብ ያለመወገን የወል ባህሪ የነበራቸው ቢሆኑም፤ የየራሳቸው ልዩ ባህሪያት የነበራቸው መሆናቸው አይካድም፡፡ ሆኖም ሰውዬው በሚገርም ሁኔታ 'ህዝባዊ የነበረው የቀድሞ ሰራዊት በሶማሊያ ዚያድ ባሬ መንግስት ወረራ ተፈጽሞብን በነበረበት ወቅት የሀገራችን ሉዓላዊነት አላስከበረምን? እናም የአሁኑ ሐውልት ይህን ሠራዊት አያካትትም ወይ?' ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

እርግጥ ሀገራችን ከጥንት ከቅድመ አያቶቻችን ጀምሮ ሀገራችን በባዕዳን ስትወረር በየወቅቱ የነበረው ሰራዊት ወይም በሰራዊትነት የተደራጀ ሃይል ሀገራዊ ሃላፊነቱን አልተወጣም ማለት አይቻልም። እናም የሰውዬው ጭንቅላት የፈጠረው ካልሆነ በስተቀር፣ በየትኛውም ስርዓት የተገነባ የመከላከያ ሃይል ሀገራችንን ከወራሪዎችና ተስፋፊዎች አልተከላከለም የሚል ሰው የለም፡፡ ወደፊትም ይኖራል ብዬ አላስብም። እናም በደርግ ወቅት የነበረው ሠራዊት ምንም እንኳን ፀረ-ህዝባዊነትን ተላብሶ የተገነባ ቢሆንም፤ ሀገራችንን ከዚያድባሬ ወረራ ተከላክሏል። ይህ የማይካድ ዕውነታ ነው። ይሁንና በመከላከያ ሰራዊቱ ቀን በምድር ኃይል ቅጥር ግቢ ውስጥ መሰረት የተጣለለት ሐውልት እርሱን የሚመለከተው አይደለም። ምክንያቱም ያ ሰራዊት ሲዋጋ የነበረው በፀረ-ህዝብነት የአምባገነኑን ስርዓት ስልጣን ለማራዘም እንጂ የህዝቡን የዘመናት የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ጥያቄዎችን ለመመለስ ባለመሆኑ ነው። እናም ሃውልቱ እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ለተዋደቁና ፈለጉን ተከትለው ህይወታቸውን ቤዛ ያደረጉ የኢፌዴሪ መከላከያ ሰራዊትን ብቻ የሚመለከት መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል።

እርግጥ በየስርዓቱ የነበሩ የመከላከያ ሰራዊቶች በሐውልት የራሳቸውን አሻራ ማኖራቸው የተለመደ ሆኖ ሳለ፤ ፀሐፊ ተብዬው የኢፌዴሪ መከላከያ ሰራዊት ሰማዕታቱን ለማስታወስ የሐውልት መሰረተ ድንጋይ ማቆሙ ምን እንዳንገበገባቸው ግልፅ ነው—ሁሉንም ነገር የመቃወም ክፉ የተቃውሞው ጎራ ደዌ። ያም ሆነ ይህ ግን በአፄ ምንሊክ የአድዋ ድል ሐውልት ላይ የአፄ ኃይለስላሴ ፊውዳላዊ መንግስት ባለቤት እንደማይሆነው እንዲሁም የጣሊያንን ዳግማዊ ወረራ የመከቱት የአጼ ኃይለስላሴ ዘመን አርበኞች ተግባር የደርግ አምባገነናዊ ስርዓት ክንዋኔ እንዳለሆነ ሁሉ፤ ህዝባዊነትን ሰንቀው ለሰላም፣ ለልማትና ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሲሉ ውድ ህይወታቸውን ቤዛ ያደረጉ ሰማዕታትን እንጂ አቶ ቴዎድሮስ ያሉትን የደርግ ሰራዊት አይመለከትም። ልክ "ድላችን" የተሰኘው የደርግ ሐውልት የአሁኑን ህዝባዊ ሰራዊት እንደማይመለከተው ማለት ነው፡፡ ነገርዬው "ያልወለድኩት ልጅ አባባ ቢለኝ..." እንዲሉት ዓይነት የታሪክ ሽሚያ ነውና።

አቶ ቴዎድሮስ "የዘንድሮው የመከላከያ ሠራዊት ይህቺን ሙሉ ሀገር (ኤርትራን ጨምሮ) የተረከበው ከሠላም፣ ከልማትና ከዴሞክራሲ አይደለም፡፡ ካለፈው የሀገር መከላከያ ሠራዊት

ላይ ነው” ባይ ናቸው። እርግጥ ይህ አባባል ሰውዬው ኤርትራን እንደ ደርግ በኃይል ለማንበርከክ ብሎም ታሪክን ለማዛባት ያላቸውን ፍላጎት የሚያሳይ ነው፡፡ መቼም ዶሮ ብታልም ጥሬዋን ነውና እዚህ ላይም በሰውዬው ቅር የሚሰኝ ያለ አይመስለኝም። እናም ሆኖም ለእርሳቸው “የዘንድሮው ሠራዊት” ያሉት የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት ሀገርን የተረከበው ከማን እንደሆነ ማሳየት ግን የሚገባ ይመስለኛል።

እንደሚታወቀው የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት ህገ - መንግስቱና ህገ - መንግስታዊ ስርዓቱን ለመጠበቅና ለማስጠበቅ ተልዕኮውን የተረከበው የሀገሪቱን ህገ - መንግስት ጸድቆ ካበቃ በኋላ ነው። ይህም የካቲት 7 ቀን 1988 ዓ.ም ነው፡፡ እርግጥ ይህ ሠራዊት ሀገሪቱን የተረከበው ሠላምና መረጋጋትን በማስፈን ለልማቱ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ከሚታትረው የሽግግር መንግስቱ ሰራዊት ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ ህገ - መንግስቱ እስኪጸድቅና ህብረ ብሔራዊ ሠራዊት እስኪቋቋም ድረስ የሀገሪቱን ሠላም ለማረጋጋት የሽግግር መንግስት ሠራዊት ተልዕኮውን ሲወጣ ቆይቶ ሲያበቃ ባይሩ የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት በህዝብ ተወካዮች አማካኝነት የሀገሪቱን ሠላም ለመጠበቅ፣ የሀገሪቱን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በማንም እንዳይቀለበስና ዘላቂ ልማት እንዲረጋገጥ የህዝብ አለኝታ ሆኖ እንዲዘልቅ ሊቋቋም ችሏል። ይህም የኢፌዴሪ መከላከያ ሰራዊት በህዝቦች ይሁንታ ላይ ብቻ የተመሰረተችውን አዲሲቷን ኢትዮጵያ የተረከበው ከሰላም፣ ከልማትና ከዴሞክራሲ ትሩፋቶች ላይ እንጂ፤ ሰውዬው በእውር ድንብሩ እንደሚያስቡት ከቀድሞው ሰራዊት አይደለም። ከቀድሞው ሰራዊት ሀገሪቱን የተረከበው የኢህአዴግ ሰራዊት እንጂ የኢፌዴሪ መከላከያ ሰራዊት አይደለም። እናም የነበረው ታሪክ ይህ ሆኖ ሳለ፣ ሠራዊቱ ሀገሪቱን ከሠላም፣ ከልማትና ከዴሞክራሲ ትሩፋቶች እንዳልተረከበ አድርጎ እያዛቡ መጻፍ ምንም ሊፈይድ እንደማይችል የደርጉን በህዝቦች ደም ያደፈ ፋይል ከመቃብሩ አውጥተውና አዋራውን አራግፈው በቅጥፈት ሊመሰክሩ የሚዳዱት ግለሰብ ሊያውቁት የሚገባ ይመስለኛል፡፡

ምንም እንኳን አቶ ቴዎድሮስ በፅሑፋቸው ላይ ያነሷቸው ሃሳቦች እርስ በእርሳቸው የሚጋጩና በአመዛኙ የኢፌዴሪ መከላከያ ሰራዊትነትን በወረቀት ላይ ለማጠልሸት ያለሙ ቢሆኑም፤ እኔ ግን አባባሎቹን ዳቦን ድንጋይ ነው ከሚሉ የተቃውሞው ጎራ የደፈና ጥላቻ

ተዋናዮች በተለያዩ ወቅቶች የሰማኋቸው በመሆኑ ከዚህ በላይ ላነሳቸው አልፈቀድኩም። ምክንያቱም በመሆኑም አንድ ዕውነታን በማንሳት ፅሑፌን ለመቋጨት ወደድኩ። እርሱም ሰውዬው እንዳሉት የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት ዕድሜ ስንት እንደሆነ ለማወቅ ምንም ዓይነት የሂሳብ ቀመር የማይጠይቅ መሆኑን ነው፡፡ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ዕድሜው ቢሰላ አስራ ስምንት ዓመት መሆኑን ማንም ያውቀዋልና፡፡ ለዚያውም በዚህች ጥቂት ዓመታት ውስጥ ታሪክ የማይዘነጋውንና በሀገራችን ታይቶ የማይታወቀው ዕድገት ዘላቂነት እንዲኖረው በቃላት ሊገለጹ የማይችሉ ታላላቅ ተጋድሎዎችን በመፈፀም አስተማማኝ ሰላምን የፈጠረ ህዝባዊ ሃይል ሆኖ። እናም ሰራዊቱ ሀገራችን በፀረ - ድህነት ትግሉ ላይ የከፈተችው ዘመቻ ለስኬት እንዲበቃና የህዳሴ ጉዟችን እንዲረጋገጥ ህገ - መንግስታዊ ተልዕኮ ለመወጣት ሁሌም ዝግጁ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ህዝብ የሚያውቀው ህዝባዊ ኃይልም በአፍቃሬ ደርግ አሉባልተኞች ስሙ ይጎድፋል ብሎ ማሰብ ትርፉ የዋህነት ብቻ ይመስለኛል። ቸር እንሰንበት።